**የሰበር መ/ቁ.** 18199

**ህዳር 7 ቀን** 1998 **ዓ.ም**

**ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ**

**አቶ አብዱልቃድር መሐመድ**

**አቶ ሐጐስ ወልዱ**

**አቶ ዳኜ መላኩ**

**አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ**

**አመልካች፡- ወ/ር ምናሴ እሸቴ**

**ተጠሪዎች፡- እነ ግርማ አያና** (7 **ሰዎች**)

*በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈፅም የቀረ ገዢ ባጋጠመ ጊዜ ኀርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ሊከተሰው ስለሚገባው ሥርዓት - የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 429*

**የአሁኑ አመልካች ፍርድ በማስፈፀም ላይ የነበረ ፍርድ ቤት ባወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት የገዛ፣ ቢሆንም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም በዚሁ መሠረት የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሎ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ይከፈል በማለት ትዕዛዝ ሊሰጥ በዚሁ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለትም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡ -**

**<u>ውሣኔ</u> ፡-የአማራ ብሐራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡**

1. **በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚቻል በሕጉ አልተመለከተም፡፡**
2. **የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 እንደሚያመለክተው ገዢው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረከ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡**





**የሰበር መ/ቁ**

**ህዳር 7 ቀን** 19

**ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ**

**አቶ አብዱልቃድር መሐመድ**

**አቶ ሐጐስ ወልዱ**

**አቶ ዳኜ መላኩ**

**አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ**

**አመልካች፡- ወ/ር ምናሴ እሸቴ ጠበቃ አፀደወይን ተክሌ ቀረቡ፡፡**

**ተጠሪዎች፡- እነ ግርማ አያና** (7 **ሰዎች**) **- የ1ኛ ተጠሪ ወኪል ቀረቡ፡፡**

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

**በዚህ መዝገብ በቀረበው የሰበር አቤቱታ የተነሣው የሕግ ጥያቄ በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል ወይም ግዴታውን ሣይፈጽም የቀረ ገኘ ባጋጠመ ጊዜ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ ፍ/ቤት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በማፅናት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ** 192/97 **ታህሣሥ** 7 **ቀን** 97 **ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡**

**ከመዝገቡ እንደሚታየው የአሁኑ አመልካች ፍርዱን በማስፈፀም ላይ በነበረው ፍ/ቤት በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት** (**ሆስፒታል**) **ገዝቶአል፡፡ ሆኖም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ የሰጠው ምክንያትም ንብረቱን ተረከብ የተባልኩት ስወዳደር ካሰብኩት እና በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ ከተመለከተው ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ** (**ተቃውሞ**) **አልተቀበለም፡፡ ይልቁንም አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሎ**

በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ይክፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የለበትምትክክል ነው ብሎአል፡፡

እንደምናየው ጉዳዩ በፍትሐብሔር ረገድ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ስለፍርድ አፈፃፀም በተመለከተ የፍትሐብሔር ሥነ - ሥርዓት ሕጉ በሰባተኛው መጽሐፍ ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጦአል፡፡ በፍርድ አፈፃፀም ንብረትን የመሸጥ ሥነ - ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ደግሞ ከቁ.422 እስከ 431 በተለይ ተቀምጠዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አሁን ለያዝነው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ቁ.429 ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያመለክተው ገዢው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ እንደሚደረግ ነው፡፡ በእርግጥ ንብረቱ እንደገና በሚሸጥበት ጊዜ ዋጋ የቀነሰ እንደሆነ በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛውና ዋጋውን ያልከፈለው ተጫራች ልዩነቱንና ኪሣራውን እንዲከፍል እንደሚገደድም ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚችል በሕጉ አልተመለከተም፡፡ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት በጥብቅ መከተል ያለበትም ሕጉን ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን ሕጉ ከሚለው ውጪ አመልካች የጨረታውን ዋጋ እንዲከፍል እና ንብረቱንም በግድ እንዲረከብ ነው የታዘዘው፡፡ ስለዚህም ትእዛዙ (አቤቱታ የቀረበበት) መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ ፣**</u>

አቤቱታ የቀረበባቸው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/ መ/ቁ. 192/97 የሰጠው ትእዛዝ እና በዚህ ትእዛዝ ፀንቶ የነበረው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡

ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው በየራሣቸው ይቻሉ፡፡



የሰ/መ/ቁ.16378

ታህሣስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡-** የ10 ዓለቃ ጌታቸው ባዩ

**ተጠሪ፡-** በቤ/ዝ/ክ/መ/ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ቅ/መ/ቤት

*ስለ ጡረታ መብት - የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኂላ ሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ስለመስራት - ድንጋጌ ቁጥር 46/53 እና አዋጅ ቁጥር 209/55 አንቀጽ 30(2)*

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኂላ ተመልሶ በመንግስት መስሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ ከወሠደ የጡረታ አበሉን መመለስ አለበት በማለት የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሠጠውን ውሳኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሳኔ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. አንድ የመንግስት ሠራተኛ በጡረታ ተገሎ አበሉን እየተከፈለው ከሆነ በሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ደሞዝ እና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል አይቻልም፡፡

2. አንድ የመንግስት ሠራተኛ በጡረታ ተገልሎ አበሉ እየተከፈለው በሌላ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጠሮ ደመወዝ ከወሰደ ከጡረታ አበሉ ወይም ከወሰደዉ ደመወዝ በመጠን የሚያነሰዉን ይመልሳል፡፡